**ከኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል (ሸንጎ)ና የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት (ENTC) ሁሉን አቀፍ የሆነ አማራጭ ኃይል ተወያይቶና ተስማምቶ ስለማቋቋም አስፈላጊነት የተሰጠ የጋራ መግለጫ**

የካቲት ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ. ም

የኢትዮጵያ ሀገራችንና ህዝባችን ሰቆቃና በደል ከጊዜ ወደጊዜ እይባሰ በመሄድ ላይ ይገኛል። የዜጎች የኑሮ ዋስትና ከዕለት ዕለት ጥያቄ ውስጥ እየገባ ነው።  ምንም እንኳን የበደሉን ጥልቀት መዘርዘር ለቀባሪው አረዱት ቢሆንም ባጭር ሀርጎች ብንጠቅስ፤ የጨቋኙና የከፋፋዩ የህውሀት ወያኔ አገዛዝ የህዝቦቿን መከባበርና አንድነት በጥላቻና በመከፋፈል ለመተካት የሚጥርበት፤ ዜጎች አላግባብ የሚታሰሩባት፣ የሚገደሉባት፤ የሚሰደዱባት፤ ነፃ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የማይካሄድባት፤ ዜጎች ከመኖሪያቸውና ከቀዬአቸው የሚፈናቀሉባት፤ ለሕግ ተገዢ ያልሆነ ፍጹም አምባገነናዊ ሥርዓት ያለባት፤ ዜጎች የገዢው ፓርቲ አባል ካልሆኑ በነፃነት ሠርተው መኖር የማይችሉባት፤ በተግባር ያልዋለ ህገ-መንግሥት ያላት፤ ከገዢው ፓርቲ ቁጥጥርና ነፃ የሆኑ የመገናኛ ብዙሀንና የማህበረሰብ ድርጅቶችና የሌሉባት፤ የኃይማኖት ነጻነት በፖለቲካ የበላይነት የሚመራባት፤ በሀገሪቱ የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት-የምርጫ ቦርድ፤ ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊሶች፤ የደህንነት መስሪያ ቤቶች፤ መከላከያና ሌሎች የገዢው ፓርቲ ፖለቲካ መጠቀሚያ የሆኑባት፤ ዜጎች  እንደ ሰው በሃገራቸው የመኖር መብቶች በሌለበት፤ የእድገት ምልክቶች ናቸው ተብለው የተሰሩ ህንፃዎችና ቤቶች በቁመታቸው ባዶ ሆነው መገኘታቸው እንደ ብሄራዊ ልማት የሚቆጠርባት፤ ወጣቶች ተምረው በሃገራቸው ሰርተው ለመኖር ስለማይችሉ የሚሰደዱባት ወዘተ ሀገር ሆናለች።

ይህች ታሪክና እውቅና የነበራት ለማደግ የምትችል አገር እየደማች ነው። ይህንን አፋኝ የአገዛዝ ስርአት በመታገል ላይ የምንገኝ ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ የማህበረሰብ ስብስቦች፤ የኃይማኖት ድርጅቶችና አባቶች፤ ታዋቂ ግለሰቦችና ያገባናል የሚሉ በሃገር ቤትና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሀገራችንን አበይት ችግሮች በመዘርዘር ብቻ ሳይሆን መፍትሄውንም ለማግኘት በተናጠልና አንዳንዴም በጋራ ከመሞከር ተቆጥበን አናውቅም። ዛሬ ሁኔታው እየተባባሰ ስለሄደ የታሪክ ሃላፊነታችን የሚጠይቀው በመፈላለግ፤ በመከባበርና በመወያየት አብሮና ተባብሮ የመስራት ጥያቄው ከመቸውም በበለጠ ደረጃ ጊዜና ፋታ የማይሰጥ ሆኖ አግኝተነዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ የሚነግረን **<u>“ለዓላማ አንድነትና ለእውነተኛ ዲሞክራሳዊ ህብረት ተነሱ” ነው።</u>**

ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤት (ENTC)ና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) አመራር ተወካዮች ሦስት ወራት ያህል የጋር ውይይቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል። በዚህ ውይይት የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በመመርመር፤ ሀገራችንን በማፈራረስና የህዝባችንን ስቃይ በማብዛት ላይ ያለውን የህወሓት አገዛዝ በማስወገድ በምትኩ ሁሉንም ወገን ያሳተፈ እውነተኛ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት በሚደረገው ትግል ያለፍንባቸውን ሂደቶች በጥንቃቄ ገምግመዋል። አንዱ የቀሰምነው ትምህርት በተበታተነ መንገድ የሚደርገው የኢትዮጵያ ትግል የሚጠበቀውና የሚፈለገውን ውጤት እንዳላስገኘና የድርጅቶችን አቅም መገንባትና የህዝብን ተሳትፎ በስፋት ሊያካትት እንዳልቻለ በተጨባጭ የሚታይ ሐቅ ሆኗል። ከዚህ በፊት ትግሉን ለማጠናከር ብዙ ትብብሮችና ቅንጅቶች የየድርሻቸውን ያበረከቱ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ትግሉን አቀናጅቶና ህዝቡን አስተባብሮ በአንድ ወጥ አመራር ሊሰጥ የሚችል ሀይል ያለመኖሩ የወቅቱ አንገብጋቢ ችግርና የአብዛኛው ህዝብ ጥያቄ ሆኗል። የችግሩ ብቸኛ መፍትሄ ይህንን አንድ ወጥ የሆነ አመራር ሊሰጥ የሚችል አካል ለመመስረት የተቃዋሚ ኃይሎች መሰባሰብና ተወያይተው ዲሞክራሲያዊ የሆነ፤ ሃላፊነትና ወደ ውጤት የሚያመራ ማእከላዊ አማራጭ መመስረት ይገባቸዋል በማለት ሁለቱ ድርጅቶች ቀደም ብለው ባደረጓቸው ስብሰባዎች ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

- ሸንጎና ሽግግር ም/ቤት በኢትዮጵያ ልኡዋላዊነት የሚያምኑና በማንኛውም የትግል ስልትና ባላቸው ሐይል ተጠቅመው ይህንን አፋኝ ስርአት የሚታገሉ ድርጅቶችን በዚህ አጀንዳ ስር ለማሰባሰብ ደረጃ በደረጃ የሁለትዮሽ ግንኙነቶች በማድረግና ከዛም ወደ ወል ግንኙነት በማሸጋገር ሰፊ የሆነ ስራ ለመሥራት ተስማምተዋል።

- የአማራጭ ኃይሉ ጠንክሮ እንዳይወጣ ማነቆ የነበሩትንና አሁንም ድረስ የሆኑትን ችግሮችና ፈተናዎች በዝርዝር ተወያይተውባቸዋል፤ እንዚህን ፈተናዎች አልፎ ለታሰበው ግብ ለመድረስ መጠቀም የሚገባቸውን ስልቶችና የፖለቲካ ጥበቦች ላይ መክረው ተስማምተዋል።

- የሸንጎና የሽግግር ም/ቤት ትብብር በራሱ ግብ አይደለም። ይህ ሂደት ተጠናቆ የታሰበው የአማራጭ ኃይል እስኪቋቋም ድረስ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች መርዳትን ጨምሮ እስካሁን በተለያዩ ዘርፎች በጋራና በግል የሚሠሯቸውን ሥራዎች ይቀጥላሉ። የነገውን እያመቻቹ የዛሬውን ተቀዳሚ ተግባሮች ተባብሮ መስራት ይገባል በሚለው መርህ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፤ ለምሳሌ የዲፕሎማሲ ስራ፤ አገር ቤት የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን የመደገፍ ስራ፤ የፖሊሲ አማራጮችን የማዘጋጀትና አገር ቤት ለሚገኙ ተወዳዳሪ ወይንም ተቃዋሚ ድርጅቶች የማቅረብ ስራ፤ የመሳሰሉትን።

- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ለዚህ በአንድ ማዕከል ለሚንቀሳቀስ ሁሉን አቀፍ የሚሆን የአማራጭ ሀይል እንደ አቅጣጭ ጠቋሚ መሪና አቅጣጫ ሰጭ (roadmap) ሆኖ የሚያገለግል ረቂቅ ሰነድ፤ ቀደም ብለው በሽግግር ም/ቤቱ ከተዘጋጀው የቻርተር ረቂቅ፤ ከሸንጎ መሪ ሰነድ፤ እንዲሁም ወደፊት አብረው ከሚጓዙ ድርጅቶችና በአገር ቤትና በውጭ ስብሰቦች የተዘጋጁ ሰንዶች ጋር ተውጣትቶና ተጨምቆ ወደፊት የሚዘጋጅ መሆኑን ስምምነት ላይ ተደርሷል።

- የማእከሉ ስያሜ ወቅቱን ጠብቆ በዚህ ዓላማ ሥር በሚሰባሰቡት ድርጅቶች ውይይትና ስምምነት የሚሰየም ይሆናል።

- ከላይ በመግቢያችን እንደተጠቀሰው በወቅቱ ከሚታየው የሀገራችን አጣዳፊ የፖለቲካ ቀውስ በመነሳት ይህንን የአማራጭ ሀይል በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት እውን ለማድረግ ሁለቱም ድርጅቶች የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግና ያላቸውን አቅምና ሀይል ሁሉ ለመጠቀም ተስማምተዋል። በዚህ አጋጣሚ መላው የኢትዮጵያ ህዝብም የራሱ አጀንዳና ፍላጎት መሆኑን ተገንዝቦ ለዚህ ዓላማ መሳካት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖና ግፊት እንዲያደርግ፤ ድምፁን እንዲያሰማ በትህትና እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤት
የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ